ቊ.2011-003 ፥ ነሐሴ ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ (August | août 2019) ።
sh1ⓐttomar.net

| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ግጥም ፤ "ከመቃብር ፡ በላይ" ፡ ዐምድ ። |
| ርእስ ፤ | "አንቺ ፡ ነሽ ፡ ሌላ ፧ የኔ ፡ ወለላ ። " |
| ደራሲ ፤ | መኰንን ፡ ተክለ ፡ አረጋዊ ። (†) |
| ዕለት ፤ | 1970 ዎቹ ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቊ.2011-003 ። |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | (ከዚህ ፡ በፊት ፡ ያልታተመ ። ) |

# ከመቃብር ፡ በላይ ።

## አንቺ ፡ ነሽ ፡ ሌላ ፧

## የኔ ፡ ወለላ ።

መኰንን ፡ ተክለ ፡ አረጋዊ [1] ።

---

ልለይሽ ፡ ተሳነኝ ፤
ዐይኔን ፡ ነው ፡ የጋረደኝ ፧
ወይስ ፡ አንቺው ፡ ነሽ ፡ የተለወጥሺብኝ ፧
ጥርስሽ ፡ ተቸምችሞ ፤
አፍንጫሽ ፡ ተጣሞ ።
ዥሮሽ ፡ ተተልትሎ ፤
እጅሽ ፡ ተጐንድሎ ።
ጉንጮችሽ ፡ ጐድጉደው ፤
አጥንቶችሽ ፡ ገጠው ።
ከንፈርሽ ፡ ተልጦ ፤
ዐይንሽ ፡ ተበልጥጦ ።
አካልሽ ፡ ሞስሙሶ ፤
ወዘናሽም ፡ ጠፍቶ ፤ ለዛሽ ፡ ተደምስሶ ።
አንቺ ፡ ነሽ ፧ ሌላ ፧
የኔ ፡ ወለላ ።
ጨርቅሽ ፡ በደም ፡ ታጥቦ ፥ መርገም ፡ በቀሚስሽ ፥
እንባ ፡ በደረትሽ ፥ ልቅሶ ፡ በልሳንሽ ፥
ሙሾ ፡ ባደባባይ ፥ ባደግንበት ፡ ግቢሽ ፤
ተገማምጦ ፡ አካልሽ ፥ በቊስል ፡ ነፍርቀሽ ፤
ሥቃይሽ ፡ በርትቶ ፥ ጠንክሮ ፡ ዋይታሽ ፤
መሳው ፡ አቈብቊቦ ፥ ጓጕቶ ፡ ለጥፋትሽ ፤
"ማለፊያ ፡ ኽነልን ፤ ይበላት!" ፡ እያለሽ ።
ልጇን ፡ የምትበላ ፡ ድመት ፡ አድርገውሽ ፥
ኹሉን ፡ መተሩና ፡ ባዶሽን ፡ አስቀሩሽ ፤
ባለጌ ፡ ደፈረሽ ፥ ጐረቤትም ፡ ጠላሽ ።
አንቺ ፡ ነሽ ፡ ሌላ ፧
የኔ ፡ ወለላ ።
የአብዮት ፡ ዕልቂት ፥ ዐሳር ፡ በየቀኑ ፤
በድን ፡ በከተማሽ ፥ ዐፅም ፡ በየደኑ ፤
ኹሉም ፡ ዐለቁብሽ ፤ ኧረ! ፡ እነማን ፡ ዳኑ ፧

---

1 በ 1970 ዎቹ ፡ በሱዳን ፡ በረሓ ፡ በጠላት ፡ የተገደሉ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የነጻነት ፡ ታጋይ ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።